PANORAMA # XL

**የትዝብት አድማ**

**ነሀሴ** 30 2000 **ዓም**

***<u>አውራ የሌለው ንብ፥ መሪ ያጣ ሕዝብ</u>***

***ንብ ያለ አውራው፥ ሕዝብ ያለ መሪው፥ ምንም ጥቅም እንደ ሌለውና የሚጠበቅበትንም ውጤት እንደማያስመዘገብ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው፡፡ በተፈጥሮ ምክንያት፥ በንብ ሠራዊትና በአውራው መካከል የለውን ግንኙነት በዝርዝር ለመናገር ባይቻልም፤ በሕዝብና በመሪ መካከል ሊኖር ስለሚገባው ሁለንተናዊ ግኑኝነት ግን ከሞላ ጎደል በዝርዝር መግለጽ ይቻላል ቢባል ስህተት አይሆንም፡፡ ብቻ፥ በንብም ይሁን በሕዝብ መካከል አንድ መሠረታዊ ትምሕርት ግን መገንዘብ ይቻላል፡፡ መምራትና መመራት፥ መርቶ ከግብ ማድራስና ተመርቶ ውጤት ማስመዝገብ፥ መርቶ ከጥቃት ማዳንና እየተመሩ ከጥቃት መዳን! ንቡ በአውራው እየተመራ አበባን ለመቅሰም መሰማራት፥ አበባን ቀስሞ ወደ ቆፎው ተመልሶ በመግባት ማር መሥራት የተፈጥሮ ሕገ ብቻ ሳይሆን፥ ተከተል አለቃህን ተመለከት ዓላማህን መባሉ፥ ከዚያም አልፎ የምርት ውጤትን ማስገኘቱን ያስተምራል፡፡***

***ኢትዮጵያ ሀገራችን፥ የአያሌ ዘመናት የመንግሥት ምሥረታ ተመክሮ ያላት በመሆኗ፥ በሕዝብና መንግሥታቱ መካከል ስለነበረው/ ስለሚኖረው ግንኙነት ለማስረዳት አንቃጣም፡፡ ብዙ ማለትም የሚያሻን አይሆንም፡፡ ነገር ግን በታሪካችን ውስጥ በተላይም በጦርነት ወቅት መሪዎች አስቀድመው ከተመቱ ፥ ሠራዊቱ ከመቅጸበት እንደሚበታተንና ሀገርም እንደሚፈታ የታወቀ ነበር፡፡ የቴዎስሮስ መቅደላ ላይ መውደቅና የዮሐንስ ገላባት ላይ መመታት በሀገሪቱና በሠራዊቱ ላይ ያስከተለውን ሁኔታ ማስታወሱ ይበቃል፡፡ በ1928ቱ የማይጨው ጦርነትም ቢሆን በጊዜው የነበሩት መሪ ከቦታው በመሰወራቸው ያስከተለውን ሁኔታ ለትምህር ማስረጃነት መጥቀሱ፥ አሁን ለአለው ሁኔታ ማገናዘቢያ የሚጠቅም ይሆናል፡፡ የመንግሥቱ ኃይለማርያም፥ ያን ሁሉ ሠራዊት ያለ መሪ ብትኖ መሸሽ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የቅርብ ጊዜ መራራ ትዝታ ሆኗል፡፡ ይህንን ሁሉ ለመንሳት የፈለግነው፥ በሀገር መሪዎችና በሕዝቡ መካከል የጠበቀ፥ የጠነከረና የተባበረ ግንኙነት ቢኖር ኖሮ፥ የቱን ያህል ሀገር እንደሚጠቀም ብሐራዊ ተግባር ማስበዝገብ የሚቻል መሆኑን ለማስገንዘብ ብቻ ነው፡፡ መንግሥቱ ኃይለመርያም ከመላው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፥ ከሠራዊቱም ጋር ጭምር በመለያየቱ ምክንያት ሀገሪቱ ዛሬ ለወደቀችበት ሁኔታ ዋና ምክንያት ሆኗል ማለት የሚቻል ነው፡፡***

***ወደ ወቅታዊው የሀገራችን ሁኔታ ስናተኩርና ፥ በዕውነት እንናገርም ካልን ደግሞ ፥ ዛሬ ለሀገር የቆመ መንግሥት አለ ብሎ የሚያምን አንድም ዜጋ እንደሌለ መገንዘብ እንችላለን፡፡ ከዚህም አልፎ ተርፎ፥ የሀገሪቱን ችግር***

ለመፍታት በመታገል ላይ ያሉት የተቃዋሚ ድርጅቶችም ቢሆን፥ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ለመረከብ ገና ብዙ ምዕራፍ መጓዝ እንዳለባቸው መገንዘቡ ከባድ አልሆነም። የተቃዋሚ ድርጅቶች ሀገራቸውን ከወያኔ የጎሳ ፖሊቲካ ለማላቀቅ የሚያደርጉት ትግል በቀላሉ የሚገመት ባይሆንም፥ አሁን ሀገሪቱ ከገጠማት ቀውስ አኳያ ማነኛቸውም ቢሆኑ፥ አመራር ለመስጠት አልመብቃታቸው ግልፅ እየሆነ ከመጣ ቆይቷል። ለዚህም አባባል እንደ ማስረጃ የሚጠቀሰው፥ ከግንቦት 97 ዓም ጀምሮ፥ የአመራር ያለህ! የመሪ ያለህ! እያለ የሚጮኸው የሕዝበ ድምፅ ነው። በአንድ በኩል፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ተቃውሞ፥ አልገዛም በማለት የሚያደርገው ሕዝባዊ አመፅ ራሱን ችሎ በመንቀሳቀስ ላይ ቢሆንም፥ በሌላ አንጻር ግን ትግሉን ከግቡ የሚያደርስለት የተባባረ ክንድ ያለው ወይም ደግሞ ራሱን ችሎ የቆመ ጠንክሮ የሚንቀሳቀስ አመራር ይፈልጋል። ይጠብቃል። ይጮኻል። ይጠይቃል። እባካችሁ ከወያኔ አገዛዝ ቀንበር አላቅቃችሁ ለፍትኅ-ርትዕ አብቁኝ ይላል። ይህ የሕዝብ ተማፅንዖና አቤቱታ መመልስ ያለበት ደግሞ የማነኛውም የተቃዋሚ ድርጅት ኃላፊነትና ግዴታ መሆን ነበረበት። እስካሁን ድረስ በተባበረም ይሁን በተናጠል የተደረገው ትግል የትም እንዳላደረሰው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ከተረዳው ዉሎ አድሯል። ለዚህም ነው መሪር አጋዛዙ ሲበዛበት በራሱ አነሳሽነት ሆ! ብሎ በመውጣት የአልገዛም ባይነቱን ኃይል በዚያ በታሪካዊው ወርሃ ግንቦት ያስመሰከረው።

የሕዝብ መነሳሳትና አመፅ ግን መሪ ከሌላው፥ አቅጣጫ ሰጭ፥ ተከላካይና ተንከባካቢ ካጣ ፥ዕድሜው ከእኩል ቀን በላይ አይሆንም። ባጭር ጊዜ ግቡን ሳይመታ ይጨነገፋል፡ ይከስማል። በአምባገነኖቹ ይጠፋል። ይህ እንዳይሆን ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች በቅድሚያ መሟላት ይኖርባቸዋል። ዋናውና የመጀመሪያው፥ የተቃዋሚ ኃይሉ ጠንካራ ኅብረት ፈጥሮ በብሔራዊ የትግል አጀንዳ መስማማት ነበር። ይህ እስካሁን ሊሳካ እንዳልቻለ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተረድቶታል። ሌላው አማራጭ የሚሆነው ደግሞ፥ ተወደደም ተጠላ፥ አንድ አስተማማኝና ጠንካራ ኃይል ነጥሮ በመውጣት ኃይልን አጠንክሮ፥ ሕዝብን አስተባብሮ በማያጠራጥር ደረጃ ትግሉን መምራት ነው፡ ይህ ደግሞ ከልብ ከታመነበትና ከግል ድርጅት ጥቅም በላይ ለኢትዮጵያ ጥቅም ከታሰበ ከባድ አይሆንም። ቁርጥኝነትና ማነኛውንም መሥዋዕት ለመከፈል ወስኖ መነሳት ብቻ ነው። ይህንን ውሳኔ አድርጎ የተነሳ ድርጅት፥ በአጭር ጊዜ ውስጥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያልተቋረጠና ያልተሸራረፈ ሙሉ ድጋፍና ትብብር እንደሚያገኝ ምንም ጥርጥር ሊኖር አይችልም።

ለኢትዮጵያ ሕዝብ እታገልለታለሁ የሚል ማነኛውም የፖሊቲካ ድርጅት፥ ከሁሉ አስቀድሞ መገንዘብ የሚገባው፥ የኢትዮጵያን መሠረታዊ ጥቅምና የሕዝቡንም አንገብጋቢ ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችለውን ብቃትና ዝግጁነት አሟልቶ መገኘቱን ነው። ሁሉም ባይሆኑ፥ አንድ አንድ የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎች፥ ከሞላ ጎደል፥ ይህን መሠረታዊ ሀቅ ይስቱታል ለማለት ባይቻልም፥ ያሏቸውን ንዑሳንም ይሁኑ ዓበይት ልዩነቶች ወደ ጎን ትተው ወያኔን ሊያርበተብት የሚችል አይበገሬ ኃይል ሆነው ለመውጣት ግን እስካሁን

አልተቻላቸውም፡፡ ይህንን ለምን እንዳላደረጉ ደግሞ የሚያወቁት እነርሱው እራሳቸው ብቻ ናቸው/ይሆናሉ፡፡ ለሕዝብ እንታገላለን እስካሉ ድረስ ደግሞ፥ የሕዝቡን ጥያቄ ለመመለስ ኃላፊነቱም ግዴታውም ከእነርሱ ትከሻ አይወርድም፡፡ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመጀመሪያው ጥያቄ፥ እባካችሁ ወስኑና አመራር ስጡን ነው፡፡ ታግላችሁ አታግሉን ነው የሚለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ፡፡ እናንት ፊታውራሪ፥ እኛ ደጅን እንሆንና ለድል አብቁን ነው የሚለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ፡፡ ወያኔን ለመጣል መጀመሪያ እናንተው ለመስዋዕት መዘጋጀታችሁን ብቻ ሳይሆን ብቃታችሁንም በተግባር አስመስክሩ ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ የሚላቸው፡፡ ተስማምታችሁ እኛን ከመራችሁን፥ ሌላውን፥ ማለት፥ ኃይሉን ጉልበቱን፤ አዕምሮውን፥ ገንዘቡን ቁሰቀቁሱን፥ መስዋዕትነቱን፥ ለእኛው ተውት ነው የሚለው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአሁኑ ወቅት፡፡ በአጭሩ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጮኸው፥ የመሪ ያለህ! ታግሎ የሚያታግል ያለህ! የአመራር ሰጭ ያለህ! ነው፡፡ ይህ የሕዝብ ጩኸት ሰሚ በማጣት ሰሎ እንዳይጠፋ አስቸኳይ መልስ ያስፈልገዋል፡፡ መልሱ ደግሞ የሚገኘው ከምዕራባውያን ሳይሆን፥ ከኢትዮጵያ የፖሊቲካ ተቃዋሚዎች ብቻ ነው፡፡ በተለይም አይከፍሉ መስዋዕት እየከፈልኩ የኢትዮጵያን ሕዝብ ነፃ ማውጣት አለብኝ ብሎ ቆርጦ የተነሳ ድርጅት ካለ!

የአሁኑን የሀገራችንን ወቅታዊ ሁኔታ ስንገነዘብ፥ ብዙ ነገሮች የተገላቢጦሽ እየሆኑ ነው፡፡ ከግንቦቱ የሕዝባዊ አመፅ መነሳሳት ወዲህ፥ ከሞላ ጎደል የምዕራባውያኑ አመለካከት በመለወጥ ላይ ይገኛል ለማለት ከሚቻልበት ሁኔታ ነው ቢባል ከዕውነት የራቀ አይመስልም፡፡ ለዚህ ባባል እንደማጠየቂያ የሚጠቀሱት፥ የሲውድን የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት፥ የአሜሪካ ኀንግረስ፥ የአወሮፓ ኅብረት፥ ጂ-8 ተብለው የሚጠሩት ባለፀጋ ሀገሮች ጉባዔና ሌሎቹም መንግሥታት፥ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ተቋማትና ለጋሽ ሀገሮች በመለስ ዜናዊ ላይ ያላቸውን ፖሊሲ እንደገና ለመመርመር እንደሚገደዱ ያወጧቸው አቋሞችና መግለጫዎች ናቸው፡፡ እንግዲህ፥ የዓለም አቀፉ ሁኔታ ይህን እየመሰለ እያለ፥ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ብዙ መስራት ሲጠበቅባቸው፥ እስካሁን የመረቃ ሥራ አልሰሩም ፡፡ አመችውን የዲፕሎማቲክ አጋጣሚ መጠቀምና ወያኔን ማስጨነቅ የሚቻለው ግን በሁሉም አቅጣጫ ሁለንተናዊ ግፊትና ተፅዕኖ ሲደረግ ነው፡፡ ትግሉን በሁለንተናዊ መልኩ ማፋፋም ከተቻለ፥ መለስ ዜናዊ ከሥልጣን ለመቆየት የሚያስችለው አንዳችም ምትኃት አይኖረውም፡፡

ዛሬ፥ የሀገራችን ሁኔታ በሁለንተናዊ መልኩ ሲታይ፥ ለትግል አመች ነው፡፡ ሕዝቡ ከዳር እስከ ዳር አልገዛም ባይነቱን በአመፅ እያስመሰከረ ነው፡፡ በበርካታ የሀገሪቱ የገጠር ግዛቶች በአያሌ ቁጥር የሚገመት ሰው በረሃ እየገባ በማመፅ ላይ ነው፡፡ አመፀኛው ፋኖ በራሱ ገፋፊነትና አነሳሽነት በራሱ መሳሪያ የራሱን ርምጃ እየወሰደ ነው፡፡ ለዚህም ትግል የሕይወት ዋጋ እየከፈለ ይገኛል፡፡ መለስ ዜናዊ የሕዝብን ሰላማዊ ተቃውሞ፥ በግድያ ለማስፈራራት ቢሞክርም፥ ይህ ርምጃው ጥንካሬውን ሳይሆን፥ የሚያሳየው የመውደቂያውን ቀን ማጣደፉን ነው፡፡፡ የዓለም አቀፉም ሁኔታ፥ የሀገር ቤቱን ትግል የሚደግፈና የሚተባባር

ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህንን ማቀናጀት የሚቻለው የተቃዋሚ ድርጅቶች እርስ በእርሳቸው ሳይከፋፈሉ ተባብረው የጋራ አመራር ቢሰጡ ነበር፡፡ ይህ እንደማይሆን የተገዘበው ሕዝብ የራሱን ርምጃ ቢወስድ የታሪክ ሃቅ በመሆኑ ማንም አይፈርድበትም፡፡ ታዲያ ይህንን ነባራዊ ሁኔታ በደንብ የተገነዘበ ድርጅት ተጨባጩን ሁኔታ ሊጠቀምበት ከቻለ ፥ የማይችልበት ምክንያት ደግሞ አይኖርም፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለሀገሩ ታላቅ ባለውለታ ከመሆኑ አልፎ ተርፎ፥ በታሪክና በትውልድ ዘንድ የሚያስመሰግን ተግባር የሚፈፅም መሆኑን ሊያውቀው ይገባል፡፡ ተወደደም ተጠላ፥ይህንን ማድረግ የሚችለው፥ ለመሥዋዕት የሚታገለው ብቻ እንደሆነ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ታምኖበታል፡፡ ይህንንም መለስና ግብረ-አበሮቹ በሚገባ ያውቁታል፡፡ ለዚህም ነው ዛሬ ይህንን መስፈርት አሟለተው ይዘዋል ብሎ የሚጠረጥራቸውን ኃይሎች ለማጥፋትና ለማሳደድ ወያኔ የተገደደው፡፡ እነዚህ አይበገሬ ኃይላት ይህን ተገንዝበው የመከላከያ ምሽጉን እያጠነከሩ፥፥ የሕዝቡን ኃይልና ሰላማወዊ አመፅ እያስተባበሩ፥ እየመሩ፥ የትግልንም አቅጣጫ እየሰጡ፥ የትግሉን አድማስ እያሰፉ፥ ሕዝብ በከንቱ እንዳይጨፈጨፍ እየተከላከሉ፥ ኃብት ንብረት ያላስፈላጊ ውድመት እንዳይደርሰበት እያደረጉ ትግሉን መምራት አለባቸው፡፡ ምዕራብያውያኑ ከመለስ ጋር ያላቸውን ዕትብት ለመቁረጥ የሚችሉት በዚህ ቆርጦ በተነሳ ኃይል የሚመራው ትግል አንድ አስተማማኝ ደረጃ መድረሱ ሲያረጋግጡ ብቻ መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡ የውጭ ከፋፋይ ኃይሎች፥ አይተውት የኃይል ሚዛኑ ወዳጋደለበት እንደሚገለበጡ ብዙ የታሪክ አጋጣሚዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የሀገራችንን ዘረፈ-ብዙ ችግር ለመቅረፍ የመጀመሪያው ርምጃ መለስን እስከ ዘረኛ ሥርዓቱ ማስወገድ ስለሆነ፥ ይህ ቆርጦ የተነሳው ኃይል የሕዝቡን ትግል ማስተባበር የመጀመሪያው ምዕራፍ ስለሆነ ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ጥሪውን ማስተላለፉን ቀጥሏል/ ይቀጥላልም፡፡

በተፈጥሮ ህግ ምክንያት ብቻ፥ ንብ ወደ አበባዎቹ ይሄዳል እንጅ፥ አበባዎቹ ወደንቡ አይሄዱም፡፡ ለመሄድም አስገዳጅ ምክንያት አይኖራቸውም፡፡ በተመሳሳይ ምክንያት፥ ቆራጥ ታጋይ ድርጅት፥ ወደ ሕዝብ እንዲሄድ፥ እንዲቀርብ፥ እንዲያደራጅና እንዲመራ የሀገራችን ጊዚያዊው ተጨባጭ የፖሊቲካ ሁኔታ የሚያስገደድው ሆኗል፡፡ ይህንን ማወቅ ደግሞ የፖሊቲካ ሀሁ ለመሆኑ ተጨማሪ ማብራሪያ የሚያሻው አይደለም፡፡ ያለዚያ ንብ ያለአውራ ሕዝብ ያለ መሪ መሆኑን ከቀጠለ ጠፍቶ ከሚቀር የመያድነው አይገኝም፡፡